የኢትዮጵያውያን ማህበር በስዊዘርላንድ

ASSOCIATION DES ETHIOPIENS EN SUISSE

ኢ.ማስ.AES
Rue H. F. Amiel 20 ; 1203 Genève
ethiopianswiss@yahoo.com

# የህዝባዊ ሰልፍ ጥሪ !
# የፈጠራ ውንጀላ ይቁም ! የታሰሩት ሁሉ ይፈቱ !

እኛ በስዊዘርላንድና አካባቢዋ የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን በኢ.ማስ አስተባበሪነት ወያኔ ስልጣን ከያዘ ከዛሬ አስራ አምስት አመት ጀምሮ በአቶ መለስ አገዛዝ አሽባሪዎች እየተጨፈጨፉ ካሉት ስማዕቶቻችን ጎን በመቆም በሀገራችን እየተካሄደ ያለውን ግፍና በደል ለአለም ህብረተሰብ በማሳወቅ የዜግነት ግዴታችንን በመወጣት በተለያየ መልክ ለመግለጽ ጥረት ስናደርግ ቆየተናል ። አሁንም ስሞኑን በቅንጅት መሪዎችና በነፃው ጋዜጠኞች አባላት ላይ እና በሌሎች ለዲሞክራሲ.ና ለህግ የበላይነት በሚ.ታገሉ ወገኖቻችን ላይ በአቶ መለስ ፍርድ ቤት በፍትህ ስም እየተካሄደ ያለውን የለዘዘ ቲያትር ለመቃወምና ለዓለም ህብረተሰብ የክሱን ሀሰተኝነት ለማሳውቅ በተለያየ መልክ ድምጻችንን አሰምተናል።

የኢትዮጵያዊያን ማህበር በስዊዘርላንድ (ኢ.ማስ) ይህን የውሸትና የተንዛዛ የፍርድ ሂደት በመቃውምና የታስሩ መሪዎቻችንና ታጋይ ጋዜጠኞችን እንዲሁም ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች በነጻ እንዲለቀቁ ለመጠየቅ በጀኔቫ ለሚገኘው ለተባበሩት መንግስታት ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነርና ለሌሎቾ አለም አቀፍ ድርጅቶች  የአቤቱታ ደብዳቤ በድጋሚ ለማስገባትና እንዲሁም የመጨረሻው የህሊና እስረኛ ከእስር እስኪ.ወጣ ድረስ ሳናሰልስ የተቃዎሞ ድምጻችንና አቤቱታ ማሰማት እንዳለብን በማመን የተቃዎሞ ሰልፍ አዘጋጅቷል።

በተለይ የተ. መንግስታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር Madam LOUISE ARBOUR April/2006 በሰጡት መግለጫ የወያኔ መንግስት የሰብአዊ መብት አያያዝ እና የመሪዎቻችን የእስር ሁኔታ በከፍረኛ ደረጃ እንዳሳሰባቸው ገልጸዋል። ስለዚህም የኮሚሽነሯ ስጋት አግባብ ያለው መሆኑን ለመግለጽና ለማጠናከር በስዊስ ከሚገኙ የተለያዩ የድጋፍ ኮሚቴዎችን ጋር የጋራ ልዑክ ኮሚሺኑ ጽህፈት ቤት ገብቶ እንዲያነጋግር ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል ።

**ለመጪው አርብ ማርች 2ቀን  በተዘጋጀው ሰላማዊ ሰልፍና የሻማ ማብራት ምሽት**
በስዊዘርላንድና በአካባቢዋ የምትገኙ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ ሻማና መፍክር ይዛችሁ እንድትገኙ ከከፍተኛ ወገናዊ አደራ ጋር ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። የታሰሩት እንዲፈቱ ለመጨኽ የዚህ ወይ የዛ ድረጅት ተከታይ መሆን አይገኖርብንም! ጨለማ ውጠን እንዳንቀር ለፍትህና ለሀገራችን ህልውና በኢትዮጵያዊነታችን ጸንተን አንድ ሆነን እንታገል! ይህ ዘግናኝ ዘረኛ ሥርዓት በኢትዮጵያዊነታችን ጸንተን ከታገልነው ታሪክ ሆኖ ያልፋል !

የህዝባችን ድምጽ ይከበር !
የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ በአስቸኳይ ይፈቱ !
ኢትዮጵያ ሀገራችን ለዘላለም ትኑር !

**ቦታው :** በዤኔቫ ሀይቅ አጠገብ በሚገኘው የተ. መንግሰታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ጽ. ቤት ፊት ለፊት - Quai Wilson 49 ; UN High Commission for Human Rights

**ቀን:** የፊታችን አርብ March 02 2007
**ሰዓት:** 14h30 — 18h30